ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ

ASSOCIATION FOR HUMAN RIGHTS IN ETHIOPIA

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ድርጅታችንን ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ ከቀን 12/03/2017 ዓ.ም ጀምሮ ከማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴ ሁሉ ማገዱን አስመልክቶ የተሰጠ አጭር መግለጫ፣

ሕዳር 14 ቀን 2017 ዓ.ም

የተከበራችሁ የድርጅታችን አጋሮች እና ብዙኋን የድርጅታችን የሥራ እንቅስቃሴዎች ተከታታዮች በሙሉ፣

ሕዳር 03 ቀን 2013 ዓ.ም በሃገር በቀል ድርጅትነት በኢትዮጵያ ውስጥ ተመዝግቦ የህግ ሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅታችን ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ፤ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን በቀን 12/03/2017 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ ላይ "ባለሥልጣን መ/ቤቱ በድርጅቱ ላይ ባደረገው የክትትልና ግምገማ ስራዎች ድርጅቱ ከፖለቲካ ገለልተኛ ሆኖ መስራት ሲገባው ከዓላማው ውጭ በመንቀሳቀስ የሃገርና የሕዝብ ጥቅምን የሚጎዱ ተግባራት ላይ በመሰማራት ከባድ የህግ ጥሰት መፈፀም" በሚል ምክንያት ከማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴ የታገደ መሆኑን አስታውቆናል። ምንም እንኳን ይህንን ድንገተኛ የሆነ ክስተትን ከባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ጋር በቅርበት በመነጋገርና በመወያየት በአስተዳደራዊ መንገድ ለመፍታት ስንል ጉዳዩን ይፋ ማድረጉን ያልመረጥነው የነበረ ቢሆንም እንኳን ዜናው በማህበራዊ ሚድያና በሌሎች መንገዶች ቀድሞ የተሰራጨ በመሆኑ በባለድርሻ አካላቶቻችን እና ብዙኋን የድርጅታችን የሥራ እንቅስቃሴዎች ተከታታዮች ዘንድ አላስፈላጊና የተሳሳቱ መላምቶችን እና መረጃዎችን ለማስወገድ ሲባል ይህንን መግለጫ ለማውጣት ተገደናል።

ድርጅታችን ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ ላለፉት አራት አመታት የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታዎችን ለማሻሻል ጥልቅ የምርምር ስራዎችን፤ በጥናት ላይ የተመሮኮዙ የውትወታ ስራዎችን እንዲሁም የመንግስት አስፈፃሚ እና ሕግ አውጭ አካላትን በሰብዓዊ መብቶች እና ሰብዓዊ መብቶችን መሰረት ያደረጉ አሰራሮች ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በማከናወን በአገሪቱ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታዎችን ለማሻሻል ለሚከናውኑ ተግባራት አጋዥ ሆኖ በቅንነትና በትጋት ሲሰራ ቆይቷል።

ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ከተቋቋመበት ዓላማ ውጪ ከላይ በተገለጹት በማናቸውም ተግባራት ላይ ያልተሳተፈ እና በፖለቲካም ሆነ በሌሎች መሰል ጉዳዮች ላይ ፍጹም በሆነ ገለልተኝነት እንዲሁም የተመሰረተበትን ዓላማ መሰረት አድርጎ እና የአገሪቱን ህጎች አክብሮ ሲንሳቀስ የቆየ መሆኑን በአጽንዖት እያረጋገጥን፤ ግልፅነት እና ተጠያቂነት ሁልጊዜም የድርጅታችን መርሆዎች ናቸው። በዚህም ሁኔታ ውስጥ ስናልፍ ለእነዚህ መርሆዎች መከበርና መረጋገጥ በከፍተኛ ሁኔታ ቁርጠኞች መሆናችንን እናረጋግጣለን።

ድርጅታችንን የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ለማገዱ በምክንያትነት ስለጠቀሳቸው ጉዳዮች ምንም ዓይነት የቀደመ መረጃና እውቀት ያልነበረው ከመሆኑም ባሻገር፣ የእግድ ውሳኔው በድርጅታችን ላይ የተላለፈው አስፈላጊ የሆኑትን የሕግ ሂደቶችን እና አሰራሮችን ሁሉ ባልተከተለና እንግዳ በሆነ መንገድ መሆኑን ለማሳወቅ እንወዳለን። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለመፍትሔ አማራጮች ከባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ጋር በምናደርጋቸው ቀጣይነት ያላቸው ንግግሮች ችግሩን ለመፍታት አስፈላጊውን ጥረት ማድረግን የምናስቀድም እና ከባለስልጣኑም በኩል ለውይይት ክፍት መሆናቸውን የገለፁልን መሆኑን ለማሳወቅ እንወዳለን። እንደሁኔታውም ሁሉንም ሕጋዊ የመፍትሔ አማራጮችን በመጠቀም እግዱ ተነስቶ ወደ መደበኛ የሥራ እንቅስቃሴችን ለመቀጠል ይቻል ዘንድ አስፈላጊ ጥረቶችን ሁሉ ማድረጋችንን እንደምንቀጥል፣ ቀጣይ ሒደቱንም ሆነ የሂደቱን ውጤት በየጊዜው እየተከታተልን፤ በግልጽነት መረጃዎችን አመቺ በሆነ መንገድ የምናደርሳችሁ መሆኑን እናስታውቃለን።

በመጨረሻም ድርጅታችን በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች በሚገባ እንዲከበሩ፤ የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ እና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን የተቋቋመበትን ዓላማ ሙሉ በሙሉ በቁርጠኝነት ለማሳካት እንደምንጥር በድጋሚ ያረጋግጣል፣ አሁንም ይህንን የገጠመንን ያልተጠበቀ ድንገተኛ እክል ከባለሥልጣኑ ጋር በመቀራረብ በውይይት በፍጥነት እንደሚፈታ እና ያለማቋረጥ ስራችንን ለመቀጠል እንደሚያስችለን በጽኑ በማመን ለዕግዱ መነሳት በምንሠራበት በዚህ አስቸጋሪ ወቅት የእናንተ ድጋፍ እና ማበረታቻ እንደማይለየን በማመን ለሚደረግልን ቀና ትብብርና ያልተቋረጠ ድጋፍ ሁሉ ከወዲሁ ከፍ ያለ የከበረ ምስጋናችንን ለማቅረብ እንወዳለን።

ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ